# ፓሪስ ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን 21ኛ ዓመት ምስረታ እና ክብረ በዓል አከባበር

**የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችበት 21ኛ ዓመት እና የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ድንግል ማርያም ዓመታዊ ክብረ በዓል ክቡር አባታችን ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ የጣሊያን እና እካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ እንዲሁም የሀገረስብከቱ ዋና ጸሐፊ ዲ/መስፍን በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል;።**

በዚህ ልዩ ታሪካዊ በዓል ከመላው ፈረንሣይ ፣ ከቤልጅየም፣ ከሆላንድ እና ከፊንላድ በመጡ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ፣ የደብር አስተዳዳሪዎች ካህናት ፤ ዲያቆናት እና መምህራን ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ምዕመን በተገኘበት ድርብ በዓሉ ተከብሯል

ደብሩ የተመሰረተበትን 21ኛ ዓመት በልዩ ሁኔታ ለማክበር ለሦስት ቀን መንፈሳዊ ጉባኤ በማዘጋጀት ከኢትዮጵያ ሰባኬ ወንጌል በማስመጣት አርብ ፣ቅዳሜ እና እሑድ ( ከግንቦት 22 – 24 ቀን 2017 ዓ.ም ) እመቤታችን ድንግል ማርያም በደብረ ምጥማቅ ለአምስት ቀናት የተገለጠችበትን በማሰብ መንፈሳዊ ጉባኤ ተደርጓል ። ይህ በአይነቱ ለየት ያለ መንፈሳዊ አገልግሎት በመሰጠቱ ብዙ ምዕመናን ደስታቸውን ሲገልጹ ተስተውለዋል።




ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ በተገኙበት ማኅሌቱ ሊቃውንቱ ነፍስ ደስ በሚያሰኝ ያሬዳዊ ዜማ በብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ እየተመራ

**"በአልባሰ ወርቅ"(፪) ዑጽፍት ወኁብርት/፪/**

**እኅትየ መርዓት ርግብየ ሠናይት እኅትየ/፪/**

በማለት ሲያመሰግኑ አንግተዋል በጥዋት የነበረውንም ቅዳሴ ብፁዕ አባታችን መሪነት ተከናውናል በተጨማሪም የመ/ሕይወት ቀሲስ ፍስሐ ተማሪዎች የነበሩ ለሁለት ታዳጊ ልጆች ማዕረገ ዲቁና በብፁዕነታቸው ተሰጥቷቸዋል።



ከቅዳሴ በኋላ በነበረው የትምህርት መርሐግብር ከኢትዮጵያ ተጋብዘው በመጡት **መምህር ዘላለም ወንድሙ** አማካይነት

ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ሉቃ ፩;፵፰ በሚል ርዕስ ዕለቱን በተመለከተ አብራርተው አስተምረዋል።



## መምህር ዘላለም ወንድሙ

የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ መልአከ ሕይወት ቀሲስ ፍስሓ ድንበሩ ባስተላለፉት መልእክት ላላለፉት 21 አመታት ስንጠቀምበት የነበረውን ይህንን ቤተ ክርስቲያን እንድንጠቀምበት ለተባበሩን የካቶሊክ ቤተ እምነት ኃላፊዎች ምስጋናቸውን አቅርበው ፤ በቦታው ለተሰበሰው ህዝበ ክርስቲያን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ዜናም አሰምተዋል መልእክታቸውን ሲቀጥሉ ዜናው እንዲህ በማለት አብስረዋል

ይህንን ላለፉት ዓመታት ስንጠቀምበት የነበረው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን የመግዛት አቅም ካላቹ መግዛት እንደምትችሉ የሚገልጽ ከራሳቸው ከቤተ ክርስቲያኑ ኃላፊዎች ለብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ በደብዳቤ ጽፈው መጠየቃቸውና ብፁዕ አባታችንም ይህንን ለሰበካ ጉባኤውና ለምዕመኑ አቅርበው መልሳቹን በደብዳቤ ልጽፍላቸው እችላለው ብለው ሲናገሩ የተሰበሰበው ሕዝብ በሙሉ ደስታም እልልታ ፈቃደኝነቱን በመግለጹ ብፁዕ አባታችን ፊት ቤተ ክርስቲያኑን ለመግዛት ቃል ተገብቷል።

በመቀጠልም ይህች ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ደረጃ አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ በጽዋ ማኅበር ተደራጅተው እንደነበርና ጽዋ ማኅበሩ ዛሬም ድረስ ያለና ይህንን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማስጀመር መሠረት የጣለ ስለሆነ ለጽዋ ማኅበሩ አባላት ምስጋናቸውን አቅርበዋ በቤተ ክርስቲያኑ ስም ለጽዋ ማኅበሩ የምስክር ወረቀት ከብፁዕ አባታችን እጅ ተቀብለዋል።



መልእከ ሕይወት ቀሲስ ፍስሐ ድንበሩ የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ

መልዐከ ሕይወት ቀሲስ ፍስሐ ድንበሩ ግብዣ ብፁዕ አባታችን ቃለ ምዕዳን እና ቡራኬን ሰጥተዋል ።


ብጹዕ አባታችን እናስተውል (ነጽጽር)

በማለት ብፁዕ አባታችን የተሰጠው ትምህርት የተነገረውን መንፈሳዊ መልእክት ማስተዋል ይገባል በማለት ምክር ሰጥተዋል። ለክርስቲያን እያንዳንዱ እንቅስቃሴው በማስተዋል ይሁን በሕይወታችን ውስጥ እየተከናወኑ ያሉትን ክንውኖች በማስተዋል እንመልከት ስናስተው እግዚአብሔር እኛን በምን መጠን ያህል እንደወደደን ፣ እንቀረበን እንረዳለን ፣በማለት አጠር ያለ ግሩም ጥዑም የሆነ መልክት አስተላልፈዋል።

ብፁዕ አባታችን በመልእክታቸው ሲቀጥሉ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ደብዳቤ እንደደረሳቸው እና መልእክቱ ይህንን ቤተ ክርስቲያን በግዢ በመልክ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጸው የደብሩ ካህናትና ሰበካ ጉባኤ እና ምዕመናን ፈቃደኛ ከሆናቹ በማለት ገና ተናግረው ሳይጨርሱ በደስታ በእልልታ ጥያቄውን መቀበላቸው ለብጹዕ አባታችን አረጋግጠዋል

ብፁዕ አባታችንም በእግዚአብሐር መንብ'ኘታችንን እናስተውል በማለት ግሩም አድርገው ካብራሩ ቦኃላ እናንተ ከወሰናቹ ሀገረ ስብከቱ በማንኛውም መልኩ ከጎናችሁ ይሆናል በማለት ድጋፋቸውን አረጋግጠዋል ።

ህዝበ ክርስቲያኑም ደስታውን በእልልታ ገልጿል።



ብጹዕ አቡነ ሕርያቆስ
የጣሊያን እና አካባቢው
ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና
የቅዱስ ሲኖዶስ አባል





ዘመን ከዘመን እየተሻገረ ሲመጣ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምዕመናን በተለያዩ ዓለም እንደመኖራቸው ለሥርዓተ አምልኮ የራሳቸውን ቦታ በግዢ መልክ በመግዛት የሕንጻ ባለቤት መሆን ከጀመሩ ሰነባብቷል በፈረንሣይም ይህን ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ግዢ በጊዜው ከተፈጸመ የመጀመሪያው ይሆናል ማለት ነው

በመቀጠል ዲ/ን መስፍን የጣሊያን እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ ቤተ ክርስቲያኗ ለምታደርገው ግዢ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐግብር አድርገዋል( በነገራችን ላይ እንደዚህ ሪፓርታዥ ዘጋቢ ከሆነ ዲ/ን መስፍን በሁሉም ቦታ በመገኘት ምዕመናን የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን እንዲኖራቸው በማስተባበር በጣም የሚድከሙና ጸጋውን የተሰጣቸው ናቸው )

ዲ/መስፍን እንኳን ደስ ያላቹ በማለት መልእክታቸውን ጀምረው ለዚህ ሕንጻ ግዢ የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ አስጀምረው 135.000 euro ገቢ አሰባስበዋል ። ይህ የገቢ ማሰባሰቢያ ወደፊትም በተለያየ መልኩ እንደሚቀጥል ከመድረኩ ተገልጿል።





በመጨረሻም ታቦተ ሕጉ ከመንበሩ ወርዶ ዑደት በማድረግ በሊቃውንተ ቤተክርስቲየን በሰንበት ት/ቤት መዘምራን ታጅቦ ከዞረ ቦኃላ ወደ መንበረ ክብሩ ተመልሷል

ላለፉት ሶስት ቀናት ዐርብ በሰርከ ጉባኤ ፣ ቅዳሜ ሙሉ ቀን በተደረገ ጉባኤ፣ እሑድም ቀጥሎ ከቁኑ 12:30 ላይ በሰላም ተጠናቋል ።

እንግዶችም የተዘጋጀውን ጸበል ጻድቅ እየቀመሱ ወደየ በዐታቸው ተመልሰዋል

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ሪፓርታዥ መ/እስክንድር ፓሪስ ፈረንሣይ